**ADDA BILISUMMAA OROMOO (ABO-WBO)**

**OROMO LIBERATION FRONT** جبهة تحرير أورومو

**Date**: *March 06, 2026* **Nr.:** *IEABO WBO/03-02/02-2026*

**Guyyaa**: *Bitootessa 06, 2026* تاريخ **Lakk.:** *IEABO-WBO/03-02/02-2026* رقم


# የአምነስቲ ሪፖርት፡ የምርመራ ውድቀት፣ የትርክት መሳሪያነት እና የአድልዎ ነጸብራቅ (የኦነግ-ኦነሠ መግለጫ)

በጾታ ላይ የተመሰረተ ጥቃት በማንኛውም ማህበረሰብ ውስጥ ካሉት እጅግ አስከፊ ወንጀሎች አንዱ ነው። በኦሮሚያ እና ከዚያም ባሻገር በመላ ሃገሪቱ በሴቶች እና ልጃገረዶች ላይ የሚደርስ ማንኛውም የወሲብ ጥቃት በግልጽ መወገዝ ያለበት፣ በተናጥል እራሱን ችሎ መመርመር እና ክስ መመስረት ያለበት ከባድ የኢፍትሃዊነት መገለጫ ነው። የትም ቢከሰት እና የፈጸመው ማንኛውም ሰው ቢሆን ተቀባይነት ሊኖረው አይችልም። በሲቪሎች፣ በተለይም በሴቶች ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎችን መካድ፣ ምክንያታዊ አድርጎ መሞገት ወይም ማሳነስም ተቀባይነት የለውም። በኦሮሚያ ውስጥ የተከሰቱት እነዚህ በደሎች ለረጅም ጊዜያት ተደብቀው የቆዩ ሲሆን፣ የችግሩ ተጠቂዎች ያሳለፉትን ስቃይ ለመመዝገብ እና ችግራቸውን ለዓለም አቀፍ ትኩረት ለማቅረብ የሚደረገውን ማንኛውንም እውነተኛ ጥረት በደስታ እንቀበላለን።

ሆኖም፣ የአምነስቲ ኢንተርናሽናል «ማንም ሊያድነኝ አልመጣም» በሚል ርዕስ ያወጣው ሪፖርት፣ ለረጅም ጊዜ ትኩረት ለተነፈጉት ከባድ ጥቃቶች ትኩረት የሳበ ቢሆንም፣ በጥልቀት ሲመረመር ከፍተኛ ጉለቶች ያሉትና ለተጎጂዎች ፍትሕን ከመፈለግ ይልቅ ሌላ ኣላማ ለመሳካት የኳተነ ሆኖ ተገኝቷል። ሪፖርቱ የጥናት ዘዴ ድክመት፣ መሠረታዊ የእውነታ ስህተቶች እና በአንዲት የተወሰነች ትኩረት ውስብስብ የሆነውን ጦርነት በአደገኛ ሁኔታ ኣቅልሎ ያቀርባል። ከሁሉም በላይ ደግሞ፣ የታጠቁ ተዋናዮች የኦሮሞ ነፃነት ሰራዊትን ተመስለው የሚፈበረኩበት፤ በሚገባ የተዘገበ ክስተት ሆኖ እያለ ይህንን ዘር ብሎ ያላየ ሲሆን ፡ ይህ እውነታ በዋሽንግተን ፖስት፣ ሮይተርስ እና በኢትዮጵያ የሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን ጭምር በተናጥል የተረጋገጠ ነው። ይህ መሠረታዊ ጉዳይ ነው። ወንጀለኞችን በአስተማማኝ ሁኔታ መለየት በማይቻልበት ጊዜ ተጠያቂነት ማስፈን በፍጹም የማይቻል ስለሚሆን። ይህ ክፍተት በሪፖርቱ ላይ መኖሩ ግን ጉዳት የደረሰባቸውን የእህቶቻችንን ስቃይ አያሳንስም። የሪፖርቱ ዋና ዋና ክፍተቶች እንደሚከተለው ቀርቧል።

## 1) ዋነኛው ኃጢአት፡ ወንጀለኞቹን መለየት አለመቻል እና «የሐሰት OLA» ኃይሎችን ፈጽሞ እንደሌሉ መቁጠር

የዚህ ሪፖርት አስከፊ ውድቀት ወንጀለኞቹን በትክክል መለየት አለመቻሉ ነው። በገጽ 15 ላይ፣ አምነስቲ የሚከተለውን በግልጽ አምኖ ይቀበላል፡ ሪፖርቱ «በታተመበት ጊዜ ማንነታቸውን(የወንጀለኞቹን) ማረጋገጥ አልቻልንም።» በእንደዚህ ዓይነት ምርመራ፣ ወንጀለኛውን መለየት ካልቻልክ፣ ወንጀል መርምረህ መደምደምያ ላይ መድረስ ይቅርና፤ ክስ መጀመርም አይቻልም። ወንጀለኛው ሳይለይ ማን ሊከሰስ ይችላል? የጦር ወንጀሎችን ለመበየን ለሚፈልግ የሰብአዊ መብቶች ሪፖርት፣ ይህ የእምነቱ ማረጋገጫ ብቻ ሪፖርትቱን

ይፋ ከማድረግ መቆጠብ የሚስችለው መሆን ነበረበት። በተጨማሪ የኣገዛዙ ቅጥረኛ የሆኑ «ሐሰተኛ የOLA ወታደሮች» መኖራቸው የተረጋገጠ እውነታ ነው። የዋሽንግተን ፖስት ምርመራ፣ ከመንግሥት ኃይሎች ጋር ግንኙነት ባለው የቀድሞ እስረኛ የሚመራው የOLAን ስም አንግቦ ሲንቀሳቀስ የነበረው ፀረ፡አማፂ ቡድን ያለ ሲሆን ይህም በOLA ላይ የሚቀርቡ የዜጎች ጥቃትና ግድያዎችን ሲፈጽም መቆየቱን ኣረጋግጧል። የሮይተርስ ምርመራ «ኮሬ ናጌኛ» (የደህንነት ኮሚቴ) የተባለውን ሚስጥራዊ ቡድን የኦሮሚያ ከፍተኛ ባለስልጣናትን እንቅስቃሴ ይፋ አድርጓል፣ ይህም ከህግ አግባብ ውጭ ግድያዎችን እና ህገወጥ እስራቶችን ያስፈጸመ ያዘዘም ነው። በወሳኝነት ምርመራው የከረዩ አባ ጋዳ ልዑካን ጭፍጨፋ የተቀነባበረው በእነዚህ ባለስልጣናት መሆኑን አረጋግጧል፣ ከዚያም የኦሮሚያ ኮሙኒኬሽን ቢሮ ግድያዎቹን ለOLA እንዲያሳብብ መታዘዙን ኣጋልጧል።

ኣምነስቲ ሪፖርቱ ውስጥ የጥቃቱ ሰለባዎች ወንጀለኞቹ ማንነታቸውን፤ OLA መሆናቸውን በግልጽ እንደነገሯቸው ይናገራሉ [ገጽ 15]። ይህ የተላላኪ ታጣቂዎች ተግባር ደምበኛ መለያ ነው። በራሳቸው በሚቆጣጠሩት ከባቢ ውስጥ ትክክለኛ የOLA ተዋጊዎች ወንጀል ሲፈጽሙ ማንነታቸውን አስቀድመው የሚናገሩት ለምንድን ነው? የተገለጸው ባህሪ መንግስት የላካቸውን አስነዋሪ ወኪሎች ግፍ እንዲፈጽሙ ብቻ ሳይኖን ስትፈጽሙ OLA ነን በሉ ተብሎ የተሰማሩ ለመሆናቸው ትልቅ ማሳያ ነው። አምነስቲ ኢንተርናሽናል ይህን በሚገባ የተመዘገበ የኣገዛዙ ታጣቂዎች እውነታን ሙሉ በሙሉ ችላ በማለቱ፣ ስህተት እየሠራ ብቻ ሳይሆን፤ በኣገዛዙ የሚደገፍ ገዳይ ቡድን ስምን በንቃት እያጠበ ጭምር ነው። የመንግስትን ፕሮፓጋንዳ እንደ ሰብአዊ መብቶች ጥናት አድርገው እያቀረቡትም ነው።

## 2) ባሕሩን የማድረቅ የኣገዛዙ ፖሊሲ፡ በሪፖርቱ ችላ የተባለ የኣገዛዙ የፀረ ሽምቅ ዶክትሪን

ሪፖርቱ የሴቶችን መፈናቀል እና ቤቶችን ማቃጠልን ይገልፃል። ነገር ግን እነዚህን ድርጊቶች ከኢትዮጵያ አገዛዝ ግልጽ እና ይፋዊ ፖሊሲ ጋር አያገናኝም። እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ የኦሮሚያ ብልጽግና ፓርቲ መሪ የነበረው ፍቃዱ ተሰማ ዓሳዎቹን ለመያዝ ባሕሩን ማድረቅ አለብን ሲል በይፋ ተናግሯል። ይህ ሲቪሉን ህዝብ (ባህሩን) ለOLA (ዓሣው) የድጋፍ መሰረት አድርጎ የሚቆጥር በይፋ የተገለጸ የኣገዛዙ የፀረ ሽምቅ ኦፍስየላዊ ዶክትሪን ነው። በሪፖርቱ ውስጥ የተገለጹት የጅምላ መፈናቀል፣ የቤቶች ማቃጠል እና ማህበረሰቦችን ማሸበር ለOLA ድጋፍ ላደረጉ ሰዎች ለመቅጣት የተደረገ የፖሊሲው ተግባራዊት መገለጫ ነው። የአምነስቲ ሪፖርት፣ ለዚህ መፈናቀል OLA ተጠያቂ በማድረግ፣ የአንድ ከፍተኛ የመንግስት ባለስልጣንን ኑዛዜ ወስዶ ለተጎጂዎቹ ክስ እንደማድረግ ነው። የሪፖርቱ የህግ ትንተና፣ «የታጠቀው ቡድን ተዋጊዎች የሲቪል ህዝብን ክፍል ለማፈናቀል የጾታዊ ጥቃት እየተጠቀሙ ነው ብሎ ማመን ምክንያታዊ ነው» [ገጽ 23]፣ የተረጋገጠ ተመሳሳይ ግብ ያለው የተመዘገበ የኣገዛዙ ፖሊሲ በመኖሩ ውድቅ ያደርገዋል።

## 3) ተዓማኒነቱን ጥያቄ ውስጥ የሚያስገቡ መሠረታዊ የሃቅ ስህተቶች

የሪፖርቱ ተዓማኒነት በራሱ መሰረታዊ የሃቅ ስህተቶች ትብታብ ስር ይወድቃል። ስለ OLA ኣደረጃጀት ማንም ተራ ሰው ሊያጣራቸው የሚችላቸውን መሰረታዊ ሃቆችን ኣያውቃቸውም። ምሳሌዎች፥

- “OLA አምስት ዋና ዋና ዕዞች አሉት» [ገጽ 11] ፡ ሐሰት። OLA በኦሮሚያ ስምንት ዕዞች አሉት።
- «የምዕራቡ ዕዝ የሚመራው በጃል ገመቹ አቦዬ ነው» [ገጽ 11] ፡ ሐሰት። ገመቹ አቦዬ የምዕራቡ አዛዥ ሆኖ አያውቅም።
- «የማዕከላዊ ዞን ዕዝ የሚመራው በጃል ጂሬኛ ነው [ገጽ 11] ፡ ሐሰት። ማዕከላዊ ዕዝ ጃል ጂሬኛ በሚባል ሰው አልተመራም።

የአምነስቲ ኢንተርናሽናል ምርመራ የዕዞቻችንን ብዛት ወይም የአዛዦችን ስም በትክክል ሪፖርት ማድረግ ካልቻለ፣ ጥልቅ ምርምራ የሚያስፈልጋቸውን የጦር ወንጀል ቢያኔዎች መስጠት እንዴት ይችላል? ይህ የሚያጠኑትን ርዕሰ ጉዳይ መሠረታዊ የሆነ ግንዛቤ አለመኖሩን የሚያሳይና እና በሪፖርቱ ውስጥ ባለው እያንዳንዱ «ግኝት» ላይ ሌላ ተጨማሪ ጥርጣሬን ያስከተለ ሆኖ ተመዝግቧል።

## 4) የተመረጠ ምልከታ፡ የስርዓቱን ከፍተኛ ጥፋተኝነት መደበቅ

ሪፖርቱ በOLA ላይ ብቻ ያተኮረ መሆኑ ብያንስ እጅግ በጣም አስገራሚ የሆነ የቸልተኝነት ድርጊት ነው። ከዛ ስያልፍ ደግሞ የኣገዛዙን ወንጀሎች የማጠብ ተግባር ነው። በኦሮሚያ የተከሰተው ጦርነት የአንድ ወገን ጉዳይ አይደለም፤ በርካታ ተዋናዮችን የሚያሳትፍ ጦርነት ሲሆን፣ በተደጋጋሚ በተደረጉ ገለልተኛ ጥናቶች፤ ኣገዛዙ ለሚደርሱ በደሎች ከፍተኛውን ኃላፊነት ይወስዳል።

- የተባበሩት መንግስታት ምርመራ እንዳመለከተው የክልል ኃይሎች (ENDF፣ ፖሊስ እና ተባባሪ ሚሊሻዎች) በ2023 በኢትዮጵያ ውስጥ ከተፈጸሙት የሰብአዊ መብት ጥሰቶች 70% የሚሆኑትን ጥቃት ፈጽመዋል። ከኣመነስቲ የ10 ተጠቂዎች ናሙና ጋር ሲነጻጸር ጥናቱ 7,103 ያካተተ ሲሆን ሁሉም መንግስታዊ ያልሆኑ የታጠቁ ቡድኖች 23% ብቻ ይከሳል።
- ተመድ በተጨማሪም በነሐሴ እና ታህሳስ 2023 መካከል ብቻ፣ በENDF የተፈጸሙ 18 የድሮን ጥቃቶች 248 የሲቪል ሰዎችን ሞት እና 55 ጉዳቶችን በማስከተል ትምህርት ቤቶችን እና ሆስፒታሎችን አውድመዋል።
- በUN ICHREE የተደረጉ ሌሎች ምርመራዎች የአገዛዙ ኃይሎች በጥቃቶች ውስጥ ያላቸውን እጅግ የጎላ ሚና በተከታታይ አሳይተዋል። አምነስቲ ኢንተርናሽናል እነዚህን አሃዞች ያውቃል። ይፋዊ ናቸው። ሆኖም የኣገዛዙን ወንጀል ኣጥቦ ሪፖርት ማዘጋጀትን መርጠዋል። ይህ ሪፖርቱን የፖለቲካ መሳሪያ እንጂ የሰብአዊ መብቶች ሪፖርት አያደርገዉም።

## 5) የምርመራ ዘዴ፡ የርቀት ምርምር እና ያልተረጋገጡ ክሶች

አምነስቲ ጥናቱ የተካሄደው በመንግስት በተጣለ የመገናኛ ብዙሃን ኣፈና ባለበት መሆኑን ያምናል [ገጽ 11]። ቃለመጠይቆችን ያደረጉት ከርቀት መሆኑን ይገልጻል[ገጽ 8] ነው። ከፍተኛ የኣገዛዙ ክትትል፤ ማስፈራራት እና ፕሮፓጋንዳ ካለበት አካባቢ፣ ከሩቅ በተደረገ ቃለ ምልልስ ላይ የተመሰረተ ጥናት፤ እንድሁም በቦታው ተገኝቶ ወንጀለኞችን፣ በቦታው ያሉ ፎሬንሲክ ማስረጃዎችን ለመመርመር ዕድል ሳይኖረው የሚደረግ ጥናት ከመጀመርያዉኑ ትርጉም ያለው መደምደሚያ ላይ ሊደርስ እንደማይችል መገመት አያዳግትም። ሪፖርቱ የተገነባው

በአሸዋ መሠረት ላይ ነው። የተጎጂዎቹ ስቃይ እውነተኛ ነው ብለን እናምናለን፣ ነገር ግን ሪፖርቱን የእህቶቻችን ፍትሕ በመደበቅ በቁስላቸው ላይ እንጨት ሰዷል። ኃላፊነት የሚሰማው የሰብአዊ መብት ድርጅት፣ «ጥፋተኞቹን ማርጋገጥ ኣልቻልኩም» እያለ፣ እንደዚህ አይነት የወደቀ ሪፖርት ሳያወጣ ቆም ብሎ፣ ጥፋተኞቹን በማረጋገጥ ለእህቶቻችን ፍትሕን በማረጋገጥ በኩል ሚናውን ይወጣ ነበር። በመሆኑም ከላይ በተጠቀሱት የገዘፉ ጉድለቶች የተተበተበውን ይህንን ምርመራ ተብዬ የፖለቲካ ጥራዝ በማጠፍ እና ይቅርታ በመጠየቅ፤ ኣምነስቲ ኣዲስ ምርመራ እንድያስጀም ጥሪ እናቀርባለን።

## 6) ለገለልተኛ ምርመራ ጥሪ

የኦሮሞ ነጻነት ሰራዊት ቀደም ሲል በእሱ ስም የተላከኩ ሌሎች በርካታ ከባድ ወንጀሎች ላይ ገለልተኛ ምርመራ እንዲደረግ በተደጋጋሚ ጥሪ አቅርቧል። እነዚህ ጥሪዎች በአብዛኛው በአገዛዙ እና ደጋፊዎቹ ችላ ተብለዋል። ይህ ገለልተኛ ምርመራን የመቃወም አካሄድ ዓለም አቀፍ የተጠያቂነትን የሚሸሽውን የአገዛዙን ሰፊ ታሪክ እና የፖሊሲ አቋም መሆኑን ያሳያል። በተለይም አገዛዙ በተባበሩት መንግስታት የሰብአዊ መብቶች ምክር ቤት፣ የዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ባለሙያዎች ኮሚሽን በኢትዮጵያ ላይ የተሰጠውን ተልዕኮ እንዲያቋረጥ ያልተቋረጠ የዲፕሎማሲ ዘመቻ አካሂዷል፣ በምርመራ ስራው መካከል መንገድ ላይ አስቁሟል። ከዚህ ዳራ አንጻር፣ OLA በምዕራብ ኦሮሚያ ውስጥ በተመዘገቡት የቅርብ ጊዜ ክሶች ላይ ብቻ ሳይሆን በሁሉም የኦሮሚያ ክልል ክፍሎች ውስጥ የተፈጸሙ ከባድ በደሎች ማስረጃዎች ባሉባቸው አጠቃላይ እና በእውነት ነጻ ምርመራ እንዲደረግ ጥሪውን በድጋሚ ያቀርባል። ተጠያቂነት ሊረጋገጥ፣ የተዛባ መረጃ መወገድ እና የተጎጂዎች ክብር እና መብቶች ሊከበሩ የሚችሉት በእንደዚህ አይነት ምርመራ ብቻ ነውና።

**የኦነግ፡ኦነሠ ከፍተኛ ዕዝ**
**መጋቢት 6, 2026**